በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና
ልማት ኮሚሽን

Addis Ababa City Government
Farmers and Urban Agriculture
Development Commission

ቀን ..........
Date

ቁጥር ..........
No.

ለ፡- ንፋስ ስልክ ክ/ከተማ አ/አ/ከ/ግ/ል/ ጽ/ቤት

ለ፡- ለሚኩራ ክ/ከተማ አ/አ/ከ/ግ/ል/ ጽ/ቤት

ለ፡- ቦሌ ክ/ከተማ አ/አ/ከ/ግ/ል/ ጽ/ቤት

ለ ፡-የካ ክ/ከተማ አ/አ/ከ/ግ/ል/ ጽ/ቤት

ለ፡- አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ አ/አ/ከ/ግ/ል/ ጽ/ቤት

ለ፡- ኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ አ/አ/ከ/ግ/ል/ ጽ/ቤት

አዲስ አበባ

ጉዳዩ ፡-የፀደቀ የድጋፍ ማዕቀፍ መመሪያ መላክን ይመለከታል

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ታህሳስ 13/2014 ዓ.ም በአንደኛ ዓመት በሦስተኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ ተወያይቶበት ውሳኔ ከሰጠባቸው ጉዳዮች አንዱ የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች የድጋፍ ማዕቀፍ መመሪያ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ስለሆነም በከተማ አስተዳደሩ ካቢኔ የፀደቀውን መመሪያ ቁጥር 02/2014 በቀን 13/3/15 በቁጥር አአከፅ /21/04/235 ከከንቲባ ፅ/ቤት በተጻፈ ደብዳቤ መመሪያው መፅደቁን ያሳወቀን መሆኑ እየገለፅን፤መመሪያ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ ተግባራዊ እንዲደረግና ሥራ ላይ እንዲውል እያሳሰብን፤ ይህ መመሪያ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ እንዲደረግና ወደ ተግባር ለመግባት ያመች ዘንድ የመመሪያውን ...... ገፅ ሰነድ ከዚህ ሸኚ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ግልባጭ

- ዋና ኮሚሽነር
- ም/ኮሚሽነር(አርሶ አደር መልሶ ማቋቋም እና ፈንድ...) ዘርፍ
- አርሶ አደር ማቋቋም ልማት ዳይሬክቶሬት
- የአርሶ አደር መቋቋም ልማት ቡድን

አ/አ/ከ/ግ/ል/ኮ

☎+251)011-1550244 E-mail-info.aabolsa @gmail.com አዲስአበባ-ኢትዮጵያ
✉ 3328 Fax- 011-155-9341 Addis Ababa-Ethiopia

ከንቲባ ፅህፈት ቤት
አዲስ አበባ,ኢትዮጵያ

Office of the Mayor
Addis Ababa,Ethiopia

624
14/3/15

ቀን 15/03/2015
Date
ቁጥር [illegible]/21/04/235
Ref.No

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የከተማ አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን፤
አዲስ አበባ፤

ጉዳዩ፡-የጸደቀ መመሪያ መላክን ይመለከታል፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ታህሳስ 13/2014ዓ.ም በአንደኛ ዓመት በሦስተኛ መደበኛ ስብሰባው ወቅት ተወያይቶ ውሳኔ ካሳረፈባቸው ጉዳዮች አንዱ የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች የድጋፍ ማእቀፍ አፈጻጸም መመሪያ አንዱ እንደሆ ይታዋቀል።

በመሆኑም ከላይ ካቢኔ ያጸደቀው ደንብ በከንቲባ ተፈርሞ የጸደቀ በመሆኑ ደንቡን እንድታሳትሙ፣ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ እንዲደረግ እና ሌሎች አስፈላጊ ተግባራት እንድታከናውኑ እናሳስባለን።

ከሰላምታ ጋር

City Government of Addis Ababa

እንዲያውቁት፡-

> ለክብርት ከንቲባ

አዲስ አበባ

# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን

## የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች የድጋፍ ማዕቀፍ

## አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 002/2014

የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን

ሰኔ 2014 ዓ.ም
አዲስ አበባ

City Government of Addis Ababa
Record & Archive

ክፍል አራት ........................................................................................................ 15

ክልከላ፣ ኃላፊነት፣ ቅሬታና አቤቱታ የማቅረብ መብት ........................................................ 15

11. የተከለከሉ ድርጊቶች ........................................................................................ 15

12. የድጋፍ ፈላጊው ኃላፊነት .................................................................................. 15

13. የድጋፍ አመቻች አካል ኃላፊነት ........................................................................... 15

14. የቅሬታና አቤቱታ የማቅረብ መብት ........................................................................ 16

15. ስለቅሬታና አቤቱታ አቀራረብ ................................................................................ 16

ክፍል አምስት ........................................................................................................ 17

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ................................................................................................ 17

16. የመተባበር ግዴታ ............................................................................................... 17

17. ተጠያቂነት ........................................................................................................ 17

18. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች ...................................................................................... 17

19. የተሻሩ እና ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች .................................................. 18

20. መመሪያን የማሻሻል ስልጣን .................................................................................. 18

21. [illegible] ተፈፃሚነት [illegible] ........................................................................ 18

22. መመሪያዉ የሚፀናበት ጊዜ .................................................................................... 18



City Government of Addis Ababa
Record & Archive

መግቢያ ........ 3

ክፍል አንድ ........ 4

ጠቅላላ ድንጋጌዎች ........ 4

1. አጭር ርዕስ ........ 4

2. መመሪያዉን ማሻሻል ያስፈለገበት ምክንያቶች ........ 4

3. ትርጓሜ ........ 4

4. የፆታ አገላለጽ ........ 7

5. የተፈፃሚነት ወሰን ........ 7

የድጋፍ ተጠቃሚዎች፣ ዓይነት እና አሰጣጥ ........ 8

7. የድጋፍ ተጠቃሚዎች ........ 8

8. የድጋፍ ዓይነቶች ........ 8

9. የድጋፍ አሰጣጥ ........ 9

9.1. ምንም ገቢ የሌላቸው እና መስራት ለማይችሉ ስለሚደረግ ድጋፍ ........ 9

9.1.1. የመሰረታዊ ፍጆታ ድጋፍ ........ 9

9.1.2. የመጠለያ ቤት ድጋፍ ........ 9

9.1.3. ነጻ የህክምናና የትራንስፖርት አገልግሎት ........ 9

9.1.4. የምክርና ተሃድሶ አገልግሎት ........ 10

9.1.5. የድጋፉ ቀጣይነት ........ 10

9.2. ገቢ ኖሯቸው ተደራጅተው መስራት ለማይችሉ አርሶ አደሮች ስለሚደረግ ድጋፍ ........ 10

9.3. ሰርተው ገቢ ማግኘት ለሚችሉ የማቋቋሚያ ድጋፍ ........ 10

9.3.1. በዘላቂነት ለማቋቋም የድጋፍ አተገባበር ........ 10

ክፍል ሦስት ........ 14

በልማት ምክንያት ለተነሱ እና ለሚነሱ አርሶ አደሮች የሚደረጉ ሌሎች ድጋፎች ........ 14

10.1. በሥራ ይዞታዎቻቸዉ ላይ የመጠቀም መብታቸዉን ማረጋገጥን በተመለከተ ........ 14

10.2. አቅምና ፍላጎት ኖሯቸዉ በኢንቨስትመንት ለሚሰማሩ ........ 14

10.3. የመሰረተ ልማትና ማህበራዊ አገልግሎት ድጋፍ ........ 14




የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰነድና ማህደር
City Government of Addis Ababa Record & Archive

## መግቢያ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ በልማት ምክንያት የተፈናቀሉ አርሶ አደሮችና ቤተሰቦቻቸውን ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ኑሮአቸዉን በማሻሻል እና እየተነሱ ያሉት የመልካም አስተዳደር ችግሮች በመፍታት ፍትሃዊ ተጠቃሚነታቸዉን ለማረጋገጥ እና አርሶ አደሩ የተሻለ የአኗኗር ደረጃ ላይ እንዲደርስ ለማስቻል፤

በልማት ምክንያት ከይዞታቸዉ የተፈናቀሉ ተገቢዉን የማቋቋም ተግባር በማከናወን ዘለቄታዊ ተጠቃሚነታቸዉን ለማረጋገጥ የሚያስችል ግልጽ የድጋፍ ማዕቀፍ መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ ነዉ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ የከተማ አስተዳደሩን ተቋማት ቅንጅታዊ አሰራርን፣ የከተማዋን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎችን፣ የመሰረተ ልማት አቅርቦቶችን፣ የልማት ተነሺ አርሶ አደሮችን ቤተሰባዊ ሁኔታ እና የገቢ ደረጃቸውን የመሳሰሉትን ከግምት ዉስጥ በማስገባት ትክክለኛና ተገቢ የሆነ ድጋፍ ማድረግ እንዲቻል ይህንን መመሪያ አዉጥቷል።

City Gover. nent of Addis Abab
Record & Archive

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች የድጋፍ ማዕቀፍ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 002/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. መመሪያዉን ማሻሻል ያስፈለገበት ምክንያቶች

- ኮሚሽኑ በአዲስ መልክ በአዋጅ ቁጥር 74/2014 መሰረት እንዲቋቋም በመደረጉ ከተሰጠዉ ተግባር እና ኃላፊነት ጋር ለማጣጣም
- ለልማት ተነሺ አርሶ አደሮች ሲደረግላቸዉ የነበረዉን ድጋፍ አሁን ካለዉ የመሰረታዊ ፍጆታዎች ዋጋ እና የመጠለያ ቤት ኪራይ ዋጋ አንጻር ማሻሻል ተገቢ በመሆኑ
- የድጋፍ አሰጣጡ በልማት ተነሺ አርሶ አደሮች መካከል ፍትሃዊ እንዲሆን ለማስቻል
- በተደጋጋሚ በአደረጃጀት ላይ ለሚቀርቡ ቅሬታዎች መመሪያዉን በማሻሻል ምላሽ መስጠት በማስፈለጉ፤

3. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1) "አስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፡፡
2) "ከተማ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤
3) "ቻርተር" ማለት የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 ነው፤
4) "ኮሚሽን" ማለት በአዋጅ ቁጥር 74/2014 መሰረት የተቋቋመ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከማዕከል እስከ ወረዳ ያሉትን የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት መዋቅር ነዉ፤
5) "ጽ/ቤት" ማለት በክፍለ ከተማና በወረዳ ደረጃ የሚገኝ የኮሚሽኑ ተወረዳዊ አደረጃጀት ነዉ፤
6) "ኮሚሽነር" ማለት ኮሚሽኑን ለመምራት በሚመለከተው አካል የተሰየመ የበላይ ኃላፊ ነው፤
7) " የአርሶ አደር ተወካይ" ማለት በልማት ምክንያት የተፈናቀሉ ተነሺ አርሶ አደሮች ሆነው የተፈናቀለውን አርሶ አደር በዘላቂነት በማቋቋም ኢኮኖሚያዊ፤ ማህበራዊና የልማት

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት
ሪከርድና ማህደር ቁ.3
City Government of Addis Ababa
Records & Archive

ፍትሐዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ከሚመለከተው አካል ጋር በባለቤትነት ለመስራት በተገቢ አርሶ አደሩ ውክልና የተሰጣቸው ናቸው።

8) "የአርሶ አደር ቤተሰብ" ማለት በቋሚነት በአርሶ አደሩ ገቢ የሚተዳደሩ ባል፣ ሚስት፣ ልጅ እና ሌሎች ህጋዊ ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉትን ያጠቃልላል።

9) "የአርሶ አደር ልጅ" ማለት የአርሶ አደሩ ልጅ ስለመሆኑ ከወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽ/ቤት የተሰጠ የልደት ምስክር ወረቀት ወይም ልጅ ስለመሆኑ ህጋዊ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል ሰው ነው፤

10) "አርሶ አደር" ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ እየኖረ ያለ ወይም ሲኖር የነበረ እና ከግብርና ስራ በሚያገኘው ገቢ ራሱንና ቤተሰቡን ሲያስተዳድር የነበረ ወይም እያስተዳደረ ያለ ማለት ነዉ።

11) "የልማት ተነሺ አርሶ አደር" ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ እየኖረ ያለ ወይም ሲኖር የነበረ እና ከግብርና ስራ በሚያገኘው ገቢ ራሱንና ቤተሰቡን ሲያስተዳድር የነበረ ወይም እያስተዳደረ ያለ ለልማት ሥራዎች ሲባል ከይዞታው የተነሳና የመሬት ይዞታውን የለቀቀ ሲሆን ቤተሰቦቹንም የሚያጠቃልል ነው።

12) "ምዝገባ" ማለት በምዝገባ፣ ልየታና መረጃ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 001/2013 መሰረት በሚቋቋመው የምዝገባ ኮሚቴ የሚከናወን የአርሶ አደሮች ምዝገባ ነው።

13) "ልየታ" ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን በሚሰጡ አገልግሎቶችና ድጋፎች ተጠቃሚ የሚሆኑ አርሶ አደርና ቤተሰቦቻቸውን በምዝገባ፣ ልየታና መረጃ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 001/2013 መሰረት በተቋቋመው ልየታ ኮሚቴ የመለየት ተግባር ነው፤

14) "የድጋፍ ተጠቃሚ" ማለት በምዝገባ፣ ልየታ እና መረጃ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 001/2013 መሰረት ተጠቃሚ እንዲሆኑ የተለዩ።

15) "መልሶ ማቋቋም" ማለት ለልማት ተብሎ በተወሰደው መሬት ምክንያት የሚያገኙት ጥቅም ለሚቋረጥባቸው ተነሺዎች ዘላቂ የገቢ ምንጭ እንዲኖራቸው ለማስቻል የሚሰጥ ድጋፍ ነው።

16) "መሠረተ ልማት" ማለት ከመሬት በላይ ወይም ከመሬት በታች ያለ መንገድ፣ የባቡር ሀዲድ፣ የቴሌኮሙኒኬሽን፣ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ የመስኖ፣ የውሃ መስመር ወይም የፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ሲሆን ሌሎች ተያያዥ ግንባታዎችንም ይጨምራል።



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ሪከርድና ማህደር
City Government of Addis Ababa
Record & Archive

17) "ምንም ገቢ የሌላቸውና መስራት የማይችሉ" ማለት በምዝገባ፣ ልየታና መረጃ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 001/2013 ከተመዘገቡት አርሶ አደሮች በልየታ ኮሚቴ በሚደረግ ግምገማ ተመዝጋቢዎች በዕድሜ፣ በአካል ጉዳት እና በጤና እክል ምክንያት ድጋፍ የሚደረግላቸውና የዕለት ፍጆታቸውን የሚሸፍኑበት ምንም ዓይነት ገቢ የሌለቸው እና መስራት የማይችሉ ማለት ነዉ።

18) "ገቢ ያላቸዉና መስራት የማይችሉ" ማለት በምዝገባ፣ ልየታና መረጃ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 001/2013 ከተመዘገቡት አርሶ አደሮች ዉስጥ በልየታ ኮሚቴ በሚደረግ ግምገማ ተመዝጋቢዎች በዕድሜ፣ በአካል ጉዳት እና በጤና እክል ምክንያት መስራት የማይችሉ እና ገቢ ያላቸዉ ድጋፍ የሚደረግላቸው ማለት ነዉ።

19) "መስራት የሚችሉ ተፈናቃይ አርሶ አደሮች" ማለት በምዝገባ፣ ልየታና መረጃ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 001/2013 ከተመዘገቡት አርሶ አደሮች በልየታ ኮሚቴ በሚደረግ ግምገማ ተመዝጋቢዎች መስራት የሚችሉና በልማት ምክንያት ከእርሻ ስራ የተፈናቀሉ በዘላቂነት መልሶ ለማቋቋም በኮሚሽኑ በተለያየ የድጋፍ ማዕቀፍ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ናቸው።

20) "መጠለያ ቤት" ማለት በአዲስ አበባ ከተማ ክልል ዉስጥ ተገንብተው የመኖሪያ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኝ እና በወረዳ አስተዳደር እውቅና ያለው ነው።

21) "የምዝገባና ልየታ ኮሚቴ" ማለት ከተለያዩ አካላት ማለትም ከኮሚሽኑ፣ ከአርሶ አደሮች፣ ከወረዳ አስተዳደር የሚወከሉ አባላት ያሉት ሆኖ ተጠቃሚ አርሶ አደሮችን ምዝገባና ልየታ እንዲያከናውን በምዝገባ፣ ልየታና መረጃ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 001/2013 የተቋቋመ ኮሚቴ ነው።

22) "ወራሽ" ማለት ስልጣን ባለው ፍ/ቤት የወራሽነት መብት የተረጋገጠለት አካል ነው።

23) "የቅሬታና አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ" ማለት በምዝገባና ልየታ ወቅት ተፈናቃይ አርሶ አደሮች ለሚያነሱት ቅሬታና አቤቱታ መርህን መሰረት አድርጎ የምዝገባና ልየታ መረጃውን በማጣራት ተገቢውን ምላሽ እንዲሰጥ ኃላፊነት የተሰጠው አካል ነው።

24) "ባለድርሻ አካላት" ማለት ከስራው ጋር በቀጥታ ግንኙነት ያላቸው የመንግስት አካላት፣ የልማት አጋሮች፣ ተጠቃሚዎች እና የህብረተሰብ ክፍሎች ያካተተ ነው።

25) "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ... ሪከርድና ማህደር ቁ.3
City Government of Addis Ababa
Record & Archive

4. የፆታ አገላለጽ

በዚህ መመሪያ በወንድ ፆታ የተደነገገው አገላለጽ የሴትንም ፆታ ያካትታል።

5. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ በልማት ምክንያት ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2013 ዓ.ም ድረስ ከይዞታቸው የተፈናቀሉ አርሶ አደሮች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

6. የመመሪያዉ ዓላማ

1. በልማት ምክንያት የተፈናቀሉ አርሶ አደሮችና ቤተሰቦቻቸውን የሥነ- ልቦና ጫናዎችን ለመቀነስ እና በግል ወይም በማኅበር ተደራጅተዉ በተቀረጸዉ እና በሚመርጡት የሥራ መስክ እንዲሰማሩ እና ሁለንተናዊ ድጋፍ በማድረግ ዉጤታማ እንዲሆኑ እና የኑሮ ሁኔታቸዉ እንዲሻሻል ማስቻል
2. በልማት ምክንያት ይዞታቸዉ የሚለቁ አርሶ አደሮች ከሚያጋጥማቸዉ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊ እና ሥነ ልቦናዊ ችግሮች ለመከላከል እና በአካባቢያቸዉ በሚካሄዱ ልማቶች ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ።
3. በልማት ምክንያት ይዞታቸዉ የለቀቁ አርሶ አደሮችና ቤተሰቦቻቸውን በዘላቂነት ድጋፍ የሚሰራላቸዉ ተብለዉ የተለዩትን በዘላቂነት ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ ነዉ።

የአዲስ አ.ከ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤ.
ሪከርድና ማህደር ቁ.3
City Government of Addis Ababa
Record & Archive

## ክፍል ሁለት

## የድጋፍ ተጠቃሚዎች፣ ዓይነት እና አሰጣጥ

7. የድጋፍ ተጠቃሚዎች

1) በልማት ምክንያት ከይዞታቸው ሙሉ በሙሉ የተፈናቀሉ አርሶ አደሮች እና የአርሶ አደር ቤተሰቦች፤
2) በማህበርና ስራ የሚተዳደሩና በከፊል በልማት ምክንያት ይዞታቸውን የለቀቁ አርሶ አደሮች እና የአርሶ አደር ቤተሰቦች፤
3) በምዝገባ እና ልየታ መረጃ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 001/2013 አንቀጽ 15 የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች ልየታ እንደተጠበቀ ሆኖ በተጨማሪም በዚህ የድጋፍ ማዕቀፍ አፈጻጸም መመሪያ መሰረት ድጋፍ ማድረግ እንዲያመች በልየታ ኮሚቴዉ አማካኝነት የተጠቃሚዎች ልየታ የሚደረግ ይሆናል።

8. የድጋፍ ዓይነቶች

1) የመሰረታዊ ፍጆታ፤
2) መጠለያ፤
3) የማብሰያ አቅርቦት፤
4) የፋይናንስ ድጋፍ፤
5) የኤክስቴንሽን አገልግሎት፤
6) የስልጠና ድጋፍ፤
7) የገበያ ትስስር፤
8) የመስሪያ ቦታ (ማምረቻ፣ ማሳያና የመሸጫ ቦታ)፤
9) የተሃድሶ እና ምክር አገልግሎት፤
10) የስራ ዕድል ማመቻቸት ናቸዉ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሪከርድና ማህደር
City Government of Addis Ababa Record & Archive

## 9.1. ምንም ገቢ ለሌላቸው እና መስራት ለማይችሉ ስለሚደረግ ድጋፍ

### 9.1.1. የመሰረታዊ ፍጆታ ድጋፍ

ሀ. ምንም ገቢ የሌላቸው መስራት ለማይችሉ አርሶ አደሮች አባወራ ወይም እማወራ ብቻ ከሆነ 2037.00 ብር ሆኖ፤ አባወራ እና እማወራ ሆነው በአንድ ላይ የሚኖሩ ከሆነ ብር 1527.00 ተጨምሮ 3564.00 ብር ፤ከአባወራና እማወራ ውጪ ለሆኑ ሌሎች የቤተሰብ አባላት ለአንድ የቤተሰብ አባል እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች ለሆኑ እና እድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ ሆነው በጤና እክልና በአካል ጉዳተኝነት ምክንያቶች በዘላቂነት ሰርተው እራሳቸውን ማስተዳደር ለማይችሉ የቤተሰብ አባላት ለአንደኛው የቤተሰብ አባል ለአንድ አባወራ ወይም እማወራ ከሚሰጠው በ32.5% በመቀነስ 1375.00 ብር ፤ለሁለተኛው የቤተሰብ አባል ለአንድ አባወራ ወይም እማወራ ከሚሰጠው በ40% በመቀነስ 1,222.00 ብር ፤ ለሶስተኛው የቤሰብ አባል ለአንድ አባወራ ወይም እማወራ ከሚሰጠው 45.7% በመቀነስ 1106.00 ብር ለአራተኛና ከዛ በላይ ለሆኑ በእያንዳንዳቸው 1000.00 ብር በመጨመር በየወሩ ድጋፍ የሚደረግላቸው ይሆናል።

ለ. የመሰረታዊ ፍጆታ የሚሰጥ ድጋፍ መጠን እንደ አስፈላጊነቱ በየዓመቱ ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ጥናት ተደርጎ የሚሻሻል ይሆናል፤

### 9.1.2. የመጠለያ ቤት ድጋፍ

ሀ. መጠለያ ለሌላቸዉ ተጠቃሚዎች በከተማ አስተዳደሩ በኩል በማስገንባት ወይንም ሌሎች አማራጮችን በመጠቀም በቋሚነት እንዲሰጣቸው ይደረጋል፤

ለ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9.1 በተራ ቁጥር 9.1.2 በፊደል ሀ የተገለጸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ መጠለያ ተዘጋጅቶ በቋሚነት እስኪሰጥ ድረስ በየወሩ ብር 6,500.00 (ስድስት ሺህ አምስት መቶ ብር) ለቤት ኪራይ የሚሆን የገንዘብ ድጋፍ ይሰጣቸዋል።

### 9.1.3. ነጻ የህክምናና የትራንስፖርት አገልግሎት

ሀ. በምዝገባ፣ ልየታና መረጃ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 001/2013 መሰረት የተለዩና ነፃ ህክምና የሚገባቸው አርሶ አደርና የአርሶ አደር ቤተሰቦች በመንግስት ህክምና ተቋማት የሚሰጡ የህክምና አገልግሎቶችን ቅድሚያ ተሰጥቷቸው በወረዳ አስተዳደር በጀት ተይዞ በጤና መድህን ዋስትና አማካኝነት በነጻ የህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፤



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሪከርድና ማህደር ቁ.3
City Government of Addis Ababa
Record & Archive

ለ. በምዝገባ ልየታና መረጃ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 001/2013 መሰረት ለተለዩና የትራንስፖርት ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ከተማ አስተዳደሩ በነጻ የመንግስት የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፤

9.1.4. የምክርና ተሃድሶ አገልግሎት

ሀ. የተሃድሶ፣ የምክር እና የስነ-ልቦና ስልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

ለ. አካል ጉዳተኛ ለሆኑ ተጠቃሚዎች የሚያስፈልጋቸውን የሰው ሰራሽ አካል ድጋፍ እና ስልጠና ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

9.1.5. የድጋፉ ቀጣይነት

ሀ. ማንኛውም የመሰረታዊ እና የመጠለያ ድጋፍ ተጠቃሚ የሆኑ ቤተሰቦች አባወራ/እማወራ ወይም እንደ ቤተሰብ ኃላፊ የቤተሰቡን የኃላፊነት ሚና ተሸክመዉ ሲጠጡ የነበሩ ከዚህ ዓለም በሞት በሚለዩበት ጊዜ ለባወራ ሞቶ እማወራ በህይወት ካለች / እማወራ ሞታ አባወራ ካለ በህይወት ያለው በፍ/ቤት ማሳወጅ ሳያስፈልገው የሚቹ ተቀንሶ ድጋፉን እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡ እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ በሟቹ ስር የሚተዳደሩ ህጻናት ካሉ በፍ/ቤት የሞግዚትነት ኃላፊነት በተሰጠዉ ሰው አማካኝነት የድጋፉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

9.2. ገቢ ያሯቸው ተደራጅተው መስራት ለማይችሉ አርሶ አደሮች ስለሚደረግ ድጋፍ

ገቢ ያሯቸው በጤና፣ በአካል ጉዳት እና በዕድሜ ምክንያት መስራት ለማይችሉተኘጺ አርሶ አደሮች በዘላቂነት ለማቋቋም 30% እና ከዛ በላይ የትርፍ ድድርሻ ሊያስገኙ ከሚችሉ አዋጭ ከሆኑ በአክሲዮን ከተቋቋሙ ድርጅቶች ተለይተዉ ለአንድ ሰው 150,000.00 ብር የሚያወጡ አክሲዮኖች(ሼር) ግዥ በስማቸው ይፈጸምላቸዋል፡፡

9.3. ስርተው ገቢ ማግኘት ለሚችሉ የማቋቋሚያ ድጋፍ

በልማት ምክንያት ይዞታቸውን የለቀቁ አርሶ አደሮችና የአርሶ አደር ቤተሰቦችን መልሶ ለማቋቋም የሚከተሉት የድጋፍ ዓይነቶች የሚሰጥ ይሆናል፡፡

9.3.1. በዘላቂነት ስለማቋቋም የድጋፍ አተገባበር

ሀ) የክህሎት ሥልጠና

1. በመረጡት የሥራ መስክ መሰረት በኮሚሽኑ አመቻችነት በቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋም ወይም በሌሎች ስልጠና በሚሰጡ ተቋማት የክህሎት ስልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡
2. ለስልጠና የሚያስፈልጉ ግብዓቶች፣ ለስልጠና እና ለሙያ ብቃት ምዘና ወጭዎች በኮሚሽኑ እንዲሟላ ይደረጋል፡፡



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት
ሪከርድና ማህደር ቁ.3
City Government of Addis Ababa
Record & Archive

3. የስልጠናው ጊዜ እስኪጠናቀቅ ድረስ ለሰልጣኞች የትራንስፖርት እና የምሳ አበል ብር 150.00 (አንድ መቶ ሃምሳ) በቀን እየታሰበ እንዲከፈል ይደረጋል።

4. በከተማ አስተዳደሩ ከመንግስት ስራ ውጭ በሚገኙ የስራ እድል አማራጮች አቅምና ችሎታ ካላቸው ተግቢውን ስልጠና እንዲያገኙ በማድረግ ቅድሚያ እንዲሰጣቸው ይደረጋል።

ለ) አደረጃጀት

1. የማቋቋሚያ ድጋፍ ተጠቃሚዎች በንግድ ህግ ወይም በህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ መሰረት ህጋዊ ሰውነት አግኝተው ድጋፉን እንዲያገኙ ይደረጋል።

2. ተደራጅተዉ ወደ ሥራ ለገቡ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ስርዓት እንዲዘረጉ፣ የኢንስፔክሽን እና የኦዲት አገልግሎት እንዲያገኙ ኮሚሽኑ ድጋፍ ያደርጋል።

ሐ) የመስሪያ ቦታ

1. አርሶ አደሮች የመረጡትን የስራ መስክ መሰረት በማድረግ የማምረቻ፣ የማሳያ እና የመሸጫ ቦታ በከተማ አስተዳደሩ በሚሰጥ ድጋፍ መሰረት ተገንብቶ ወይም ተዘጋጅቶ እንዲሰጣቸዉ ይደረጋል።

2. በመንግስት ወጪ የሚገነቡ የመስሪያ ቦታዎች አቅርቦት በሚገቡት ዉል መሰረት ለተጠቃሚዎች በማስተላለፍ በቋሚነት የሚሰጥ ይሆናል።

3. የመሬት ይዞታቸው ተወስዶባቸዉ የተወሰነ ይዞታ ያላቸው አርሶ አደሮች በከተማ አስተዳደሩ የመሬት ልማትና አስተዳደር መመሪያ በሚፈቅደው መሰረት ቀሪ ይዞታቸዉ ላይ በመረጡት የስራ መስክ እንዲሰማሩ የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት በግል ወይም በጋራ ተደራጅተዉ መገንባት እንዲችሉ ይደረጋል።

4. በራሳቸዉ ቀሪ ይዞታ ላይ የማምረቻና የመሸጫ ቦታ በመገንባት ወደ ስራ መግባት ለሚፈልጉ አርሶ አደሮች እና ልጆቻቸው የግንባታ ፈቃድ እንዲያገኙ አስፈላጊው ድጋፍ ይደረጋል።

5. የመሬት ይዞታቸውን ሙሉ በሙሉ የለቀቁ አርሶ አደሮች በመረጡት የስራ መስክ ተሰማርተዉ ገቢ ማግኘት እንዲችሉ የከተማ ፕላን በሚፈቅደው መሰረት በከተማ አስተዳደሩ የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት በጋራ ተደራጅቶ መገንባት እንዲችሉ ቦታ የሚሰጣቸዉ ይሆናል።

6. ካፒታል ኖሯቸው መሬታቸው ሙሉ በሙሉ ለልማት ያስረከቡ በኢንቨስትመንት ሥራ መሰማራት ለሚፈልጉ አርሶ አደሮች የሚያቀርቡትን የንግድ ሥራ ዕቅድ



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሪከ
ሪከርድና ማህደር ቁ.3
City Government of Addis Ababa
Record & Archive

መነሻ በማድረግ ቅድሚያ ተሰጥቷቸው በመነሻ የሊዝ ዋጋ የመስሪያ ቦታ መሬት በከተማ አስተዳደሩ የሚሰጥ ይሆናል።

7. በራስ ይዞታ ላይ የማዕድን ማውጣት፣ አፈር ማስደፋት፣ ጠጠር ማምረት፣ ካባ ሥራ የመሳሰሉት ሥራዎች በራሳቸው ዓቅም ወይም ተደራጅተው አቅም ካላቸዉ ጋር በመቀናጀት እንዲሰሩ ይደረጋል።

8. አርሶ አደሩ በሚኖርበት አካባቢ ያሉ ክፍት ቦታዎች፣ የወንዝ ዳርቻዎች፣ የፓርኪንግ ቦታዎች ወ.ዘ.ተ ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ተደራጅተው በራሳቸዉ ወይም በጋር በመቀናጀት እንዲሰሩ ይደረጋል።

9. በልማት ይዞታቸውን ለለቀቁ አርሶ አደሮች የመስሪያ ቦታ ተገንብቶ እንዲሰጣቸዉ እና የመስሪያ እና መሸጫ ቦታዎች እና ሌሎች አማራጮች ከሚመለከታቸዉ ጋር እንዲመቻችላቸዉ ይደረጋል።

መ) የፋይናንስ ድጋፍ

1. በተለያዩ የስራ መስኮች ለመሰማራት ፍላጎት ላላቸዉ ተጠቃሚዎች ተጠንቶ በሚቀርብ የንግድ ሥራ እቅድ መሰረት ለሥራ ማስኬጃ፣ ለማሽነሪ እና ቁሳቁስ ማሟያ የሚሆን በቀጥታ ድጋፍ እና በብድር አቅርቦት የፋይናስ ድጋፍ እንዲያገኙ ይደረጋል።

2. መንግስት በሚያመቻችላቸዉ ወይም በራሳቸዉ ቀሪ ይዞታ ላይ ግንባታ በማካሄድ ወደ ስራ ለመግባት በማኑፋክቸሪንግ ወይም በከተማ ግብርና ዘርፍ ወደ ሥራ ለሚገቡ በኅብረት ሥራ አዋጅ 10 አባላት ሆነው ለተደራጁ 3,000,000.00፣ ከ10 በላይ ሆነዉ ለሚደራጁ ማህበራት በአባላት ቁጥር በእያንዳንዳቸዉ 200,000.00 /ሁለት መቶ ሺህ/ ብር በማስላ በ3,000,000.00ብር ላይ በመጨመር ድጋፍ የሚደረግላቸዉ ይሆናል።መንግስት በሚያመቻችላቸዉ ወይም በራሳቸዉ ቀሪ ይዞታ ላይ በሚያመቻቹት የመስሪያ ቦታ ከከተማ ግብርና እና ከማኑፋክቸሪንግ የሥራ ዘርፎች ዉጭ በኅብረት ሥራ አዋጅ ተደራጅተዉ ወደ ሥራ ለሚገቡ 10 አባላት ላላቸዉ 2,500,000.00፣ ከ10 በላይ ሆነዉ ለሚደራጁ ማህበራት ከአስር በላይ በሆኑት አባላት ቁጥር በእያንዳንዳቸዉ 200,000.00 /ሁለት መቶ ሺህ/ ብር በማስላ በ2,500,000.00ብር ላይ በመጨመር ድጋፍ የሚደረግላቸዉ ይሆናል። በንግድ ህጉ 5 ሆነው ለተደራጁ 1,500,000.00 ብር ሲሰጣቸው እና ከዚያ በላይ ከስድስት እስከ ዘጠኝ ላሉት አባላት በየአንዳንዳቸዉ አባል ልክ 200,000.00 ብር



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤ
ሪከርድና ማህደር ቁ.3
City Government of Addis Ababa
Record & Archive

በመጨመር ድጋፍ ይደረግላቸዋል ። በግል መስራት ለሚፈልጉ ብር 150,000.00 ወደ ሥራ እንዲገቡ የገንዘብ እና ሙያዊ ድጋፍ እንዲያገኙ ይደረጋል። ከሁለት እስከ አራት ለሚደርሱ አባላት ከሆነ በ150,000.00 ብር ላይ 175,000.00ብር በእያንዳንዳቸዉ በመጨመር ድጋፍ ይደረግላቸዋል ።

3. የሚቀርበው የንግድ ሥራ ዕቅድ አጠቃላይ ወጪ ኮሚሽኑ በዚህ መመሪያ መደገፍ ከሚችለው በላይ ከሆነ ተጠቃሚዎች የራሳቸውን ሃብት ጨምረው ወደ ሥራ መግባት ይችላሉ።

4. የፋይናንስ ድጋፍ የሚቀርብበት አግባብ

4.1. የሚሰጠዉ የፋይናስ ድጋፍ በቀጥታ ድጋፍ እና በብድር የሚሰጥ ሆኖ አፈጻጸሙን በተመለከተ

4.1.1. በጸደቀላቸዉ የንግድ ሥራ እቅድ መሰረት የፋይናንስ ድጋፉ 50% በቀጥታ ድጋፍ 50% በብድር ይሰጣል።

4.1.2. የብድር አመላለስን በተመለከተ ለአንድ ዓመት የችሮታ ጊዜ የሚሰጣቸዉ ሆኖ ብድር ተጠናቆ የሚከፈልበት በንግድና አገልግሎት ዘርፎች ለተሰማሩ በሁለት ዓመት ዉስጥ በማንፋክቸሪንግ እና በከተማ ግብርና ለተሰማሩ አራት ዓመት ዉስጥ ተመላሽ የሚደረግ ይሆናል።

4.1.3. ለመስሪያና ለተንቀሳቃሽ የሚሰጥ የፋይናንስ ድጋፍ ከአዲስ ካፒታል እቃ ፋይናስ ንግድ ስራ አክሲዮን ማህበር ከፋይናንስ ቢሮ ጋር በሚደረገው የሥራ ስምምነት ተግባራዊ ይደረጋል።

4.1.4. በብድር የሚቀርብ የፋይናንስ ድጋፍ በአዲስ ብድርና ቁጠባ ኢ.ማ ወይም በሌሎች በጥናት ተረጋግጦ ከተመረጡ የፋይናንስ ተቋማት ከፋይናንስ ቢሮ ጋር የሥራ ስምምነት በመፈራረም ተግባራዊ ይደረጋል።

4.1.5. የፋይናንስ ድጋፉ አሰጣጥ ዉጤታማ በሆነ መልኩ ማከናወን ይቻል ዘንድ ኮሚሽኑ አዘጋጅቶ በሚያቀርበዉ ፋይናስ ቢሮ፣ አዲስ ብድርና ቁጠባ ኢ.ማህበር እና ከአዲስ ካፒታል እቃ ፋይናስ ንግድ ስራ አክሲዮን ማህበር በጋራ ሆነዉ በሚያጸድቁት የአተገባበር የመግባቢያ ሰነድ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል።

የአዲስ አ.ባ ከተማ አስተዳደር ...
ሬኮርድና ማህደር ...
City Government of Addis Ababa
Record & Archive

## ክፍል ሦስት

## በልማት ምክንያት ለተነሱ እና ለሚነሱ አርሶ አደሮች የሚደረጉ ሌሎች ድጋፎች

10. ለአርሶ አደሮች እና ቤተሰቦቻቸዉ የሚደረጉ ድጋፎች

10.1. በቀሪ ይዞታቸዉ ላይ የመጠቀም መብታቸዉን ማረጋገጥን በተመለከተ

1. በተሰጣቸዉ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በይዞታቸው ላይ የማልማት መብት እንዲፈጠርላቸው ከሚመለከተዉ ተቋም ጋር በቅንጅት ይሰራል፡፡

10.2. አቅምና ፍላጎት ኖሯቸዉ በኢንቨስትመንት ለሚሰማሩ

1. በቀሪ ይዞታቸዉ ላይ ኢንቨስትመንት ለማካሄድ አቅም ያላቸዉ በሚያቀርቡት ፕሮጀክት ጥናት ጥያቄ መሰረት ታይቶ ይዞታቸዉን እንዲያለሙ ከሚመለከታቸው አካላት እንዲፈቀድላቸዉ ይደረጋል፡፡
2. አርሶ አደሮች ለሚያቀርቡት ፕሮጀክት የሚፈቀድላቸዉ መሬት መጠን በከተማዉ ለዘርፉ በተቀመጠዉ ስታንዳርድ ይሆናል፡፡
3. በራሳቸው ይዞታ ላይ ኢንቨስት ለማድረግ የፋይናንስ አቅም እጥረት ያለባቸዉ አርሶ አደሮች በሚያቀርቡት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከባንክ ብድር እንዲያገኙ ይመቻቻል
4. በራሳቸው ይዞታ ላይ በማህበር ተደራጅተዉ በኢንቨስትመንት ለመሰማራት አቅምና ፍላጎት ካላቸዉ ከሌሎች አካላት ጋር በመቀናጀት ኢንቨስት ማድረግ የሚችሉ ሲሆን ዝርዝሩ በሌላ መመሪያ ይወጣል፡፡

10.3. የመሰረተ ልማትና ማህበራዊ አገልግሎት ድጋፍ

1. ተነሺ አርሶ አደሮች በሚኖሩበት አካባቢ የሚገኙ የመሰረተ ልማትና ማህበራዊ አገልግሎት አቅርቦት እንዲሻሻል ተገቢዉን ክትትል ማድረግ፤
2. የመሰረተ ልማትና ማህበራዊ አገልግሎት ችግሮች በሚመለከተው ባለድርሻ አካል ተዘጋጅተው እና በእቅድ ተይዘዉ ደረጃ በደረጃ እንዲሟሉ ሁኔታዎችን ይመቻቻል፤
3. የመሰረተ ልማት ማሟላት ሂደት ከልየታ እስከ ትግበራ የአርሶ አደሩን ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት ባረጋገጠ መልኩ እንዲተገበር ይደረጋል፡፡

የአዲስ አ ባ ከተማ አስተዳደር ...
ሪከርድና ማህደር ...
City Government of Addis Ababa
Record & Archive

## ክፍል አራት

### ክልክል፣ ኃላፊነት፣ ቅሬታና አቤቱታ የማቅረብ መብት

11. የተከለከሉ ድርጊቶች

1. በተሰየው የፕሮጀክት የስራ መስክ ከአንድ ጊዜ በላይ በተለያዩ የስራ መስኮች ላይ ለመሳተፍ ለመደራጀት መሞከር እና ተሳትፎ መገኘት፣
2. በልማት ምክንያት ተነሺ አርሶ አደር ሳይሆኑ እንዲሁም በዚህ መመሪያ የተቀመጡትን መስፈርቶች ሳያሟሉ ድጋፍ ለማግኘት መሞከር፤
3. ከዚህ የድጋፍ አጠቃቀም መመሪያ ጋር አባሪ ሆነው ከቀረቡት የምዝገባና የፍላጎት ማሳወቂያ ቅጾች ውጪ በሌላ ቅፅ ወይም ፎርም መረጃን ሞልቶ ማቅረብ፤
4. የኮሚሽኑን መመሪያዎች እና አሰራሮች በተዛባ መልኩ መግለጽ እና ሥራ ላይ ማዋል፤
5. ኮሚሽኑ ለሚጠይቃቸው መረጃዎች ህጋዊ ድጋፎች በወቅቱ ያለማሟላትና ተገቢውን ትብብር ያለማድረግ ክልክል ነው።

12. የድጋፍ ፈላጊው ኃላፊነት

1. ተጠቃሚው ድጋፍ ለማግኘት በቅድሚያ በዚህ መመሪያ የተቀመጠውን መስፈርት አሟልቶ በማንባር ወይም በህጋዊ ወኪሉ አማካኝነት መቅረብና ትክክለኛ መረጃ መስጠት ይኖርበታል።
2. በኮሚሽኑ የሚሠጡትን ማስረጃዎች በአግባቡ የመያዝና በተጠየቀ ጊዜ የማቅረብ፤
3. በተጠቃሚነቱ የሚሰጡትን ድጋፎች በአግባቡ የመጠቀም ፤
4. ማንኛውም የድጋፍ ማዕቀፍ ተጠቃሚ በድጋፍ አሰጣጥ ሂደት ሕገ-ወጥ ድርጊቶችና ከመመሪያው ውጭ እየተፈጸሙ ያሉ ተግባራቶች ካጋጠሙት ጉዳዩን ለኮሚሽኑ ወይም ለሚመለከተው አካል የመጠቆም እና የማስረዳት፤
5. በኮሚሽኑ ተጠቃሚ እንዲሆን የተለየ አካል ኮሚሽኑ በወሰናቸው ጊዜ እና ቦታ የድጋፍ ጥያቄ ማቅረብ ግዴታ አለበት፤

13. የድጋፍ አመቻች አካል ኃላፊነት

1. ድጋፍ አመቻቹ ስለአመዘጋገብ ሂደት፣ስለ ፕሮጀክቶቹ ዓይነት፣ ስለአማራጭ የስራ መስኮች እንዲሁም ስለ ድጋፍ አሰጣጥ ስርዓት በቅድሚያ ለድጋፍ ጠያቂው በቂ መረጃ መስጠት አለበት፣



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ...
ሪከርድና ማህደር ...
City Government of Addis Ababa
Record & Archive

2. ስለቅጾች አሞላል፣ ስለማመልከቻ አቀራረብ፣ ስለኃላፊነት፣ ስለተጠያቂነት እና ስለመልሶ ማቋቋም ዓላማ በቂ መረጃ ለተጠቃሚዎች ገለጻና ድጋፍ የመስጠት፣
3. ለድጋፍ አገልግሎት በምዝገባና ልየታ መመሪያ የተሰበሰቡ አርሶ አደሮችን መረጃዎች በማደራጀት ለድጋፍ ሰጭ አካል ያስተላልፋል በየወቅቱም መረጃዎችን ወቅታዊ በማድረግ ያሳውቃል ፤
4. በምዝገባ፣ ልየታና መረጃ አያያዝ መመሪያ እና በድጋፍ ማእቀፍ ማስፈጸሚያ መመሪያዎች ለድጋፍ አገልግሎት ተለይቶ ባቀረበው ጥያቄ መሰረት ድጋፍ ሲመቻች በተጠቃሚው በሚሞላ መነሻ ቅጽ ፋይል እንዲከፈት ይደረጋል፤
5. ቅሬታ ለሚያቀርቡ ተገልጋዮች አፋጣኝ የሆነ ምላሽ የመስጠት ኃላፊነት አለበት፤
6. ተመዝጋቢዎች ስለመመዝገባቸው እና ስለታቀፉበት ድጋፍ ማዕቀፍ የሚያስረዳ ወይም የሚያረጋግጥ ማስረጃ ደረጃውን የጠበቀ የምዝገባ ማስረጃ መታወቂያ ወይም ሰርተፊኬት መስጠት ይኖርበታል፤
7. የተመዝጋቢዎችን የድጋፍ አገልግሎት አሰጣጥ መረጃ ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ ማድረግ ይኖርበታል።

14. የቅሬታና አቤቱታ የማቅረብ መብት

ማንኛውም የዚህ የድጋፍ ማዕቀፍ መመሪያ ተጠቃሚ ከሂደቱ ጋር ተያይዞ የሚነሱ ቅሬታዎችን በቅድሚያ ለወረዳ ወይም ለከተማ ጽ/ቤቱ፣ ለክፍለ ከተማው የቅሬታ ሰሚ አካል በወቅቱ የማቅረብ መብት አለው። ቅሬታው ካልተፈታለት ለኮሚሽኑ እና በየደረጃዉ ላለ የፍትህ አካል ማቅረብ ይችላል።

15. ስለቅሬታና አቤቱታ አቀራረብ

በማቋቋሚያ ድጋፍ ማዕቀፍ እና ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ የሚቀርብ ቅሬታና አቤቱታ በመንግስት የቅሬታና አቤቱታ አፈታት ሥርዓት መሰረት የሚፈጸም ይሆናል።

City Government of Addis Ababa
Record & Archive

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

16. ልዩ ልዩ ድጋፎች ስለሚደረጉበት አግባብ፤

1. በሚመለከታቸው ተቋማት የጤና፣የትምህርት ፣የባህል፣የትራንስፖርት እና ሌሎች መሰረተ ልማቶች በእቅድ ተይዘው እንዲሟሉ ይደረጋል ።
2. በዚህ መመሪያ እንዲሰጡ ከተወሰኑ ድጋፎች በተጨማሪ ሌሎች ልዩ ልዩ ድጋፎች ሲገኙ በኮሚሽኑ አቅራቢነት በከተማው አስተዳደር እየተወሰነ እንዲሰጥ ይደረጋል።

17. የመተባበር ግዴታ

* ማንኛውም ሰው ይህን መመሪያ ለማስፈጸም የመተባበር ግዴታ አለበት።

18. ተጠያቂነት

1. ማንኛውም ተጠቃሚ በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩትን አንቀፆች በመተላለፍ ለድጋፍ የተመዘገበ፣ለመመዝገብ የሞከረ፣ ያሳሳተ፣ የድጋፍ ሂደቱን ያወከ፣ ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት የሞከረ፣ ሀሰተኛ ሰነድ ያቀረበ እንደሆነ እና የዚህን መመሪያ ድንጋጌ የተላለፈ በሀገሪቱ የወንጀል ህግ እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች መሠረት ተጠያቂ እንዲሆን ስልጣን ላለው አካል በኮሚሽኑ በኩል ክስ እንዲቀርብበት ይደረጋል፣

2. በዚህ መመሪያ የተጣለውን ግዴታ ያልተወጣና ክልከላዎችን የጣሰ ማንኛውም አስፈጻሚና ፈጻሚ ሰራተኛ ከሆነ በሀገሪቱ የወንጀለኛ ህግ ድንጋጌዎች ተጠያቂነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንግስት ሠራተኞ አዋጅ ቁጥር56/2010 መሠረት በዲሲፕሊን ቅጣት እንዲከሰስ ይደረጋል፣

19. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

ይህ መመሪያ በከተማ ካቢኔዉ ጸድቆ ከመዉጣቱ በፊት በሥራ ላይ ዉለዉ የነበሩት መመሪያዎች መሰረት የተሰጡ ህጋዊ ዉሳኔዎች እና የተፈጸሙ ሥራወች ተፈጻሚነታቸዉ የተጠበቀ ነዉ ።



የአዲስ አ [illegible] ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት
ሪከርድና ማህደር ቁ.3
City Government of Addis Ababa
Record & Archive

20. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

21. መመሪያ የማሻሻል ስልጣን

ይህን መመሪያ ማሻሻል ሲያስፈልግ ኮሚሽኑ ሊያሻሽል ይችላል።

22. የትርጉም አሻሚነትን በተመለከተ

በዚህ መመሪያ የተገለጹ ቃላቶች እና ዐርፍተ ነገሮች አሻሚ ትርጉም የሚሰጡ ሆነዉ በተገኙ ጊዜ ኮሚሽኑ የሚሰጠዉ ትርጉም የመጨረሻ ትርጉም ተደርጎ ይወሰዳል።

23. መመሪያዉየሚፀናበትጊዜ

ይህ መመሪያ ከ ሰኔ 2014 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

ሰኔ 06/2014 ዓ.ም

አዳነች አቤቤ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ

የአዲስ አ.ባ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤ.
ሪከርድና ማህደር ቁ.3
City Government of Addis Ababa
Record & Archive